# የመስቀሉ ነገር

ከ፲፪ኛው ገጽ የዞረ

ራ ከተቀበረበት ጉድጓድ ካወጣችው በኋላ መስቀሉን በማግኘትዋ ወሰን የሌለው ደስታ ተሰምቷት ነበር ፤ ከደስታዋም የተነሣ ወድያውኑ በመስቀሉ ስም ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽበት መስቀሉ ተቀብሮበት ከነበረው ቦታ ላይ የመሠረት ድንጋይ አኑራለች።

ስለዚህ መስቀሉ የተገኘበት፡ከተቀበበረበትም ተቆፍሮ የወጣበት መጋቢት 10 ቀን 327 ዓ.ም. ሲሆን የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ግን መጋቢት ተጀምሮ መስከረም 17 ቀን ሥራው ተፈጽሞ ቤተ ክርስቲያኑ ተመርቆ መስቀሉ ስለ ገባ ነው የመስቀል ቅዳሴ ቤቱ ብለን ባመት ባመት በደመቀ ሥነ ሥርዓት ስናከበረው የምንኖር።

መስቀል ሰይጣን ድል የተነሣበት ጠላታችንም የሚሸነፍበት ስለ ሆነ የመስቀልን ነገር ከማሰብ ወደ ኋላ ማለት የለብንም ያለ መስቀል ሌላ ትምክህት አይኑረን ፡ ከክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ ተብሎ ተጽኋልና።

ከነፈረግብ ማርቆስ